የከ/መ/ቁ 282549
ህዳር 09 ቀን 2013 ዓ/ም

ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት
ልደታ ምድብ 4ኛ ንግድ ችሎት

ዳኛ፡- መካ ነስሩ
ከሣሽ፡- አቶ ኢብራሂም ሚፍታህ - ከጠበቃ ተማም አባቡልጉ ጋር ቀረቡ
ተከሣሾች፡- 1 - ዶ/ር ናስር ዲኖ
2 - አቶ ጀማል መዘይን
3 - አቶ አህመድ ሁሴን ጠበቃ አብድልሐኪም ጀማል ቀረቡ
4 - ዶ/ር ኢድሪስ መሐመድ
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ብይን ተሠጥቷል፡፡

ብ ይ ን

ለዚህ ብይን መነሻ የሆነው ከሳሽ ጥር 13 ቀን 2012 ዓ.ም አሻሽለው ባቀረቡት ክስ ተከሳሾች በምስረታ ላይ ያለው የዘምዘም ባንክ አክሲዮን ማህበር መስራች አባላት ሆነው የተመዘገቡ ወይም እየተንቀሳቀሱ ያሉ ናቸው፡፡ ከሳሽ በማህበሩ ምስረታ ላይ አስፈላጊ የሆኑ ምክረ ሃሳቦችን አዋጥቷል፣ ጽፏል ፤ ከተከሳሾች ጋር በመሆን ህግ እንደወጣ የሚጠበቅበትን ሁሉ አድርጓል፡፡ ዘምዘም ባንክ ተፈቅዶ ሲመሰረት ግን ተከሳሾች ከሳሽን የማህበሩ መስራች አባል አላደረጉትም፡፡ በመሆኑም ከሳሽ የዘምዘም ባንክ መስራች አባል ነው ተብሎ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 307(4) መሰረት እንዲወሰንልን፤ የአክሲዮን ማህበር መስራች (አደራጅ) አባል መሆን በራሱ ብቻውን ጥቅም ያስገኛል፤ ተከሳሾችም ጥቅም አግኝተዋል፡፡ ተከሳሾች በማህበሩ መሰራችነት ያገኙትን ጥቅምና የከሳሽን ድርሻ እና ከሳሽ በተከሳሾች ድጊት የደረሰበትን ጉዳት አይነት እና መጠን ለይቶ ባወቀ ጊዜ ካሳ ለማስከፈል በተከሳሾች ላይ ክስ የማቅረብ መብቱ እንዲጠበቅለት እና በግልጽ ይቅርታ እንዲጠይቁ እንዲታዘዝልኝ እንዲሁም በዚህ ክስ ምክንያት ያወጣሁትን ወጪ እና ኪሳራ እንዲተካልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሾችም የከሳሽ ክስ ደርሷቸው የካቲት 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ከሳሽ ክስ ባቀረቡበት ጉዳይ ላይ የሚጠየቀው ዳኝነት ቢሰጠው የሚያስገኝለት ጥቅም ወይም መብት ስለሌለው የክስ ምክንያት የለውም፡፡ ከሳሽ ለማህበሩ መቋቋም እንዲጸና ያደረጉት እርምጃ የለም እንጂ ካለ እንኳ ለሶስተኛ ወገኖች ሃላፊ ይሆናሉ እንጂ ለማህበሩ መዋጮ ሳያደርጉ ወይንም በማህበሩ መመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ ላይ ከትርፍ ልዩ የተካፋይነት መብት ሳይረጋገጥላቸው በፍርድ ቤት ስለጠየቁ ብቻ የሚያገኙት ነገር ስለሌለ የክስ ምክንያት የሌለው ነው ተብሎ ክሱ ውድቅ ይደረግልን፡፡ አንድ ሰው የአንድን ማህበር ሼር ለመግዛት ሳይፈርም እና ገንዘብ ሳያዋጣ መስራች አባል ሊሆን አይችልም፡፡ አደራጅ አባልነት ለማስወሰን የሚልም በየትኛውም ህግ የተቀመጠዳኝነት ሊጠየቅበት የሚችል መብት የለም፡፡ ስለዚህ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 231 መሰረት የማያስከስስ ነው ተብሎ በነጻ እንድንሰናበት እንዲሁም ከሳሽ ገና ባልተመሰረተና ባለአክሲዮን ባልሆኑበት ማህበር ላይ ተከሳሾች ሊሰጧቸው የሚችሉት ጥቅም ባለመኖሩ በተከሳሾች ላይ ክስ ለማቅረብ አይችሉም ሲል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(3) እና 244(2(መ)) መሰረት ክሱን ውድቅ ያድርግልን በማለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በተከሳሾች የቀረቡትን መቃወሚያዎች እና በከሳሽ የቀረበው አስተያየት አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበው መቃወሚያ የክስ ምክንያት የለውም በሚል ሲሆን ለዚህም በምክንያትነት የተጠቀሰው ከሳሽ መስራች ልሁን ብለው ስለጠየቁ ብቻ በፍርድ ቤት

የሚረጋገጥላቸው መብት እና ጥቅም የለም፤ በክሳቸው ላይ ያረጋገጡት መብት እና ጥቅም የለም፤ ተከሳሾች የሚሰጡት ጥቅም የለም እንዲሁም ይህንን አይነት ውሳኔ መስጠት የሚችለው ጠቅላላ ጉባኤ ነው እንጂ ፍርድ ቤት አይደለም በሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረቡትን ምክንያቶች ከህጉ አንጻር የመረመረው ሲሆን

በመሰረቱ የክስ ምክንያት የሚለው ሐረግ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 29፣80(2)፣ 224(2)፣ 231(1(ሀ)) ያሉትን ድንጋጋዎች በማየት በሕጉ መካተቱን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ቢሆንም ተጠቃሽ ድንጋጌዎቹም ሆነ ሌሎች አግባብነት ያላቸው የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች ስለሐረጉ ግልፅ ትርጓሜ አላስቀመጡም፡፡የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33 ድንጋጌ ይዘት ሲታይ ማንም ሰው በሕግ ችሎታ ኖሮት በሌላ ሰው ላይ ማናቸውንም ክስ ለማቅረብ እንዲችል አስቀድሞ ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ነገር ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑ መረጋገጥ እንደሚገባው ሲያስቀምጥ ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለውም ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ሊፈፀም የሚችል መብት አለኝ ብሎ ለማለት አስቀድሞ ለመብቱ መገኘት መነሻ የሆነውን ነገር በማረጋገጥ የተጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ከሳሽ በሕግ መብት ያለው መሆኑን እንደሚኖርበት ነው፡፡

ከፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርኣት ሕግ ቁጥር 80(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መመልከት የሚቻለው ክስ ምክንያት ሲባል አንድ ሰው አንድን ነገር ከአንድ ሰው ላይ ለማግኘት ፍርድ ቤቱ እንዲወስንለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው ፍሬ-ነገር ሁኔታ መሆኑን፣ ይህም ፍሬ-ነገር ዳኝነት ለማግኘት የሚያስችል መሆን ያለበት መሆኑን ነው፡፡ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች የክስ ምክንያት አለ ብሎ ለመወሰን የሚቻለው በክሱ ላይ የቀረበው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሹ የጠየቀው ዳኝነት ለማግኘት ሕግ ይፈቅድለታል ወይ? ለሚለው ጥያቄ አውንታዊ ምላሽ መስጠት ሲችል መሆኑን ነው፡፡ይህ ስለመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 16273 በቀረበለት ጉዳይ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ስለሆነም የክስ ምክንያት አለ ብሎ በአንድ ክስ ለመወሰን በክሱ ላይ የቀረበው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሹ የጠየቀው ዳኝነት ሕጉ የሚፈቅድለት መሆኑን ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ይህ ሁኔታ ክስ እንደቀረበ ወዲያውኑ ወይም በፍሬ-ነገር በማስረጃ ሲነጥርም የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡ የክስ ምክንያት የሚለይበት የክርክር ደረጃ የተለያየ መሆኑን መገንዘቡ ተገቢ ሲሆን ይህንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተከራካሪ ወገኖች የመደመጥ መብትም በጥንቃቄ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ይሆናል፡፡

የከሳሽ በክሳቸው ላይ ዳኝነት የጠየቁት መስራች አባል ልሆን ይገባል በሚል ሲሆን አክሲዮን ማህበር ሲቋቋም እንደ መስራች አባል የሚባሉት እነማን እንደሆኑና መስራች አባል በመሆናቸው ያለባቸውን ኃላፊነት እና ሊያገኙ የሚችሉት ጥቅምም በንግድ ህጉ አንቀጽ 307 እና ተከታዮቹ ድንጋጌ ተዘርዝሮ ይገኛል፡፡ ተከሳሾች በክሳቸው ላይ ሊያገኙ የሚችሉትን መብት እና ጥቅም አላረጋገጡም በሚል ያቀረቡትን መከራከሪያ በተመለከተ ከተጠየቀው ዳኝነት አንጻር መስራች አባል ሊሆኑ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጉዳይ የፍሬ ነገር ክርክር ሲደረግ የሚታይ ሆኖ መስራች አባል መባላቸው ግን ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም እንዳለ በህጉ ላይ ስለ ትርፍ ወሰን እና ስለወጡ ወጪዎች መተካት በተቀመጡት ድንጋጌዎች ላይ መስራች አባላት ሊያገኙ የሚችሉት ጥቅም እንዳለ ስለሚያሳይ ሊያረጋግጡት የሚችሉት ጥቅም የለም ሊባል አይችልም፡፡

ከሳሽ ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ላይ የተጠቀሱት ፍሬ-ነገሮች በክርክር ሂደት በማስረጃ ቢረጋገጡ ከሳሽ በምስረታ ላይ ያለው ማህበር አደራጅ መሆናቸው ተረጋግጦ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችል ጉዳይ በመሆኑና ይህም በሕግ ክልከላ የተጣለበት ጉዳይ ስላልሆነ ክስ የቀረበበት ጉዳይ የክስ ምክንያት የለውም አያስብልም፡፡

በሌላ በኩል መስራች ሊባል ይገባል አይገባም የሚለውን ጉዳይ መወሰን የሚችለው ጠቅላላ ጉባኤ ነው የሚለውን በተመለከተ በንግድ ህጉ ቁጥር 307 ላይ መስራች አባላት እነማን እንደሆኑ ለይቶ በዝርዝር አስቀምጧል። ይህንኑ በዝርዝር ከተቀመጡት መመዘናዎች አንፃር ከሳሽ በምስረታ ላይ ያለው ዘምዘም ባንክ አክሲዮን ማህበር እውን መሆን ያደረጉት አስተዋፅኦ መኖሩ ቢረጋገጥ በንግድ ህጉ ቁጥር 307(4) መሰረት በአደራጅነት (በመስራችነት) መቀበል ሲገባው ከሳሽን ሳይቀበል ቀርቷል የሚል ዳኝነት ከቀረበ በሕጉ የተመለከተው መመዘኛ በፍርድ ቤት ተሟልቶ የተገኘ መሆን አለመሆኑን ፍርድ ቤት ሊወስነው የሚችል ጉዳይ ነው።

ሁለተኛው የቀረበው መቃወሚያ ተከሳሾች ሊሰጧቸው የሚችሉት ጥቅም ስለሌለ እንዲሁም ተከሳሾች ላይ ክስ ለማቅረብ የሚስችል ግንኙነት ስለሌለን ተከሳሾች ላይ ክስ ማቅረብ አይችሉም የሚል ነው።በአንድ ጉዳይ ላይ ከሣሽ የሆነ ሠው ተከሣሽ አድርጐ ባቀረበው ሠው ላይ ከሚጠይቀው ከህግ ወይም ከውል የመነጨ መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን ሳያረጋገጥ እንዲሁም በማናቸውም ሠው ላይ ክስ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33(3) ሥር ተመልክቷል።በኢትዮያ የንግድ ሕግ ቁጥር 307 ሥር የሚቋቋመው አክሲዮን ማህበር በንግድ ሕግ ቁጥር 317 መሰረት አክሲዮን በግልፅ ለሕዝብ እንዲሸጥ በማድረግ የሚቋቋም ከሆነ መስራቾች የሚባሉት የማህበሩ መግለጫ (ፕሮስፔክተስ) የሚፈርሙት፣ ለማህበሩ በዓይነት መዋጮ የሚያደርጉ ወይም ከትርፉ ላይ ልዩ ተከፋይነት እንዲኖራቸው መብ ያላቸው እንዲሁም በማህበሩ ያልገቡ ማንኛውም ሰው የማህበሩ መቋቋም እንዲፀና ሲሉ ማንኛውም እርምጃ እና ለማህበሩ ስራ ያደረጉ ሁሉ የአክሲዮን ማህበሩ መስራቾች እንደሚሆኑ ደንግጓል።

ተከሳሾች የዘምዘም ባንክ አክሲዮን ማህበር ለመመስረት በማህበሩ አደራጅነት እየተንቀሳቀሱ መሆኑ አልተካደም።ተከሳሾችም ይህን በተመለከተ ያስተባበሉትም ሆነ የተቃወሙት ነገር የለም።በንግድ ህጉ ቁጥር 308 ላይ በምስረታ ወቅት አክሲዮን ማህበሩ ተቋቁሞ የራሱ የየሕግ ሰውነት ያለው ባለመሆኑ አደራጆች ለሚቋቋመው አክሲዮን ማህበር ብለው የሚገቧቸው ውሎች ለሦስተኛ ወገን ገንዘብ ጠያቂዎች በኃላፊነት የሚጠየቁ መሆኑን የተመለከተ ሲሆን በቁጥር 309 ሥር የማህበሩ ካፒታል ሙሉ በሙሉ እንዲገዛና ለማቋቋሚያውም አስፈላጊው ገንዘብ ገቢ ስለመሆኑ፣ በዓይነት የተደረጉት መዋጮዎች በአግባቡ ስለመገመታቸው እና ስለማህበሩ አቋቋም ለሕዝብ ያቀረቡት ማስታወቂያ እርግጠኛ ለመሆኑ መስራቾች የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተደንግጓል።

በተያዘው ጉዳይ ከሳሽ ዳኝነት የጠየቁት በምስረታ ሂደት ላይ ያለው ዘምዘም ባንክ አክሲዮን ማህበር መስራች አባል (አደራጅ) መሆናቸው ፍርድ ቤት አረጋግጦ እንዲወስንላቸው እና ተከሳሾች በአክሲዮን ማህበሩ መስራችነት ካገኙት ጥቅም የከሳሽን ድርሻ እንዲከፍሉ እንዲሁም ወደ ፊት በተከሳሾች ላይ ክስ አቅርበው ለመጠየቅ መብት እንዲጠበቅላቸው ነው።

ከላይ በዝርዝር ከተቀመጡት ድንጋጌዎች አንፃር የሚቋቋመው አክሲዮን ማህበር በንግድ ሕግ ቁጥር 307 መሰረት አክሲዮን በግልፅ ለሕዝብ እንዲሸጥ በማድረግ የሚቋቋም ከሆነ ለማህበሩ ምስረታ ሐሳብ ጠንሰሰው ለማስፈፀም የሚተጉትንና አክሲዮን ማህበሩ ለመመስረቱን ሐሳብ ጠንሰሰው የሚተጉት ሰዎች ለማህበሩ ምስረታ የሚቀጥሯቸው ሰዎች ጭምር አደራጆች በንግድ ሕጉ አገላለፅ መስራቾች መሆናቸው መረዳት የሚቻል ቢሆንም በማደራጀት ሂደት ላይ ማህበሩ ሳይቋቋም በአደራጆች መካከል መስማማት አለመኖሩ ወደ ፊት ለሚቋቋመው ማህበር መስራች (አደራጅ) የመሆን መብት ሌሎች አደራጆች እውቅና ስላልሰጡ ፍርድ ቤት እውቅና ይስጥልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ በአንድ በኩል ወደ ፊት ያልተመሰረተው (ያልተቋቋመው) አክሲዮን ማህበር ቢቋቋም ላቋቋሙት እና ለመስራቾች ሊጠብቅ የሚችለው የትርፍ ክፍያም ሆነ በማቋቋም ሂደት ላይ የወጣ ወጪን በተመለከተ ቀርቦ ክርክሩን ሳያሰማ ውሳኔ መስጠት በመሆኑ በሌላ በኩል በምስረታ ሂደት ላይ ያለን የአክሲዮን ማህበር አደራጆችም ሆኑ በሕጉ

የመስራችነት መብት አላቸው የተባሉት ሰዎች ኃላፊነታቸው ነው ተብሎ በሕግ ተለይቶ ከተቀመጠው ውስጥ የማህበሩ አደራጅ ሊሆን የሚችል ሰው በአደራጅነት አልያም በመስራች አባልነት እውቅና መስጠትም ሆነ መቀበል የጋራ ኃላፊነታቸው መሆኑ አልተመለከተም፡፡
በመሰረቱ ከሳሽ በክስ ማመልከቻቸው ላይ ለዘምዘም ባንክ አክሲዮን ማህበር መመስረት ያደረጉት አስተዋፅኦ መኖሩንና ይህ አስተዋፅኦ የአደራጅነት መብት አልያም የመስራችነት መብት ሊያስገኝላቸው የሚችል ከሆነ መብቱ ሊጠየቅ የሚችለው እና የሚበስለው የአክሲዮን ማህበሩ መቋቋም እውን ሲሆን ነው፡፡ ስለሆነም ከሳሽ ዳኝነት የጠየቁበት ጉዳይ ላይ ከተከሳሾች የሚጠይቁት መብት አለመሆኑ ስላልተረጋገጠ እና ከተከሳሾች የሚጠይቁት መብት መኖሩ ያላረጋገጡ በመሆኑ ከሳሽ ያቀረቡት ክስ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33(3) እና 244(2(መ)) መሰረት ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም ተከታዩ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. ከሳሽ ከተከሳሾች ላይ የሚጠይቁት መብት ወይም ጥቅም መኖሩን ያላረጋገጡ እና ተከሳሾች ክስ የቀረበበት ጉዳይ የማይመለከታቸው በመሆኑ የቀረበው ክስ ፍርድ ቤቱ ውድቅ አድርጎታል፡፡
2. ከሳሽ ያቀረቡት ክስ በቀረቡት መቃወሚያዎች ውድቅ ስለተደረገ በዚህ ችሎት በነበረው ክርክር ምክንያት የወጣ ወጪና የደረሰ ኪሳራ የሚያሳይ ዝርዝር ተከሳሾች በከሳሽ ላይ የማቅረብ መብት ተጠብቋል፡፡
3. ይግባኝ ለጠየቀ ወገን መዝገቡ ተገልብጦ ይሰጥ፡፡
መዝገቡ በብይን እልባት ስላገኘ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡
የማይነበብ የዳኛ ፊርማ አለበት፡፡